# በራሪ ወረቀት - ቀጣይነት ያለው የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የሚጣል መመሪያ

## ቀጣይነት ያለው የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የሚጣል መመሪያ ምንድን ነው?

አንዳንድ ሰዎች እንደ ርእሰ መምህራን እና የትምህርት እና ስልጠና መምሪያ ሰራተኞች 'የተፈቀደላቸው ሰዎች' ይባላሉ። ወደ ትምህርት ቤቱ ሲሄዱ ወይም ከትምህርት ቤቱ ጋር ማንኛውንም ግንኙነት ሲፈጽሙ ሊከተሉዋቸው የሚገቡ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን አላቸው።

መመሪያው ወደ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ወደሚደረጉባቸው ሌሎች ቦታዎች እንዳይገቡ ወይንም እዛ ቦታ እንዳይቆዮ ሊያግዱዎት ይችላል። መመሪያው እርስዎ ከተወሰኑ ሰዎች ጋር በተወሰነ ስአት፣ በትምህርት ቤት ወይም በሌሎች የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች በሚደረጉባቸው ቦታዎች ሲገናኙ ማሳየት የሚገባዎትን የተወሰነ ባህሪ በግልጽ ሊያስቀምጥ ይችላል። መመሪያው ተግባራዊ የማይሆንባቸውን እንደ ጊዜ ወይም ቦታዎች ያሉ ልዮ ሁኔታዎችን ዝርዝር ሊያካትት ይችላል።

መምህራን፣ ተማሪዎች እና ሌሎች በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ሰዎች የደህንነት ስሜት እንዲሰማቸው ለማድርግ ይህ መመሪያ ተጥሎብዎታል። የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ስለሚጣሉ መመሪያዎች ተጨማሪ መረጃ እዚህ ማግኘት ይችላሉ። የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ስለሚጣሉ መመሪያዎች ለመረዳት እንዲያግዝዎት ቪዲዮውን እዚህ መመልከት ይችላሉ።

## መመሪያው ለምን ያህል ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል?

እነዚህ ደንቦች ለምን ያህል ጊዜ ተግባራዊ እንደሚሆኑ መመሪያው በተጨማሪ ይገልጽልዎታል። መመሪያው ከ12 ወራት በላይ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም።

## ሊጣልብኝ በታሰበው መመሪያ ላይ ተቃውሞ ካለኝ ይህንን ለትምህርት ቤቱ እንዴት ላሳውቅ እችላለሁ?

የተፈቀደለት ሰው ቀጣይነት ያለውን መመሪያ እርስዎ ላይ ከመጣሉ(ሏ) በፊት ቀጣይነት ያለው መመሪያ እርስዎ ላይ ለመጣል እያሰቡ እንደሆነ እና ለምን ይህንን መመሪያ ለመጣል ያሳሰባቸውን ምክንያት ማሳወቅ አለባቸው። ለተፈቀደለት ሰው የተቃውሞ ደብዳቤ ማስገባት ይችላሉ። በዚሁ ደብዳቤ ውስጥ በጊዜው ለምን በዚህ መንገድ ያሳዮትን ባህሪ እንዳሳዮ አብራርተው፣ መመሪያው እርስዎን ወይም ልጅዎን በምን መልኩ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድርባቹህ ወይም ሌላ ማወቅ የሚያስፈልጋቸውን ነገር አካትተው በማንኛውም ጊዜ ማስገባት ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ልጅዎ አካል ጉዳተኛ መሆኑን ለተፈቀደለት ሰው ነግረው ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ መደገፍዎን መቀጠል እንዲችሉ እንዲሁም ይህንን እንዲደግፉ ሊያደርጓቸው ይችላሉ።

የተፈቀደለት ሰው መመሪያውን እርስዎ ላይ ለመጣል እያሰቡ እንደሆነ ከነገሩዎት በኋላ በ7 ቀናት ውስጥ ተቃውሞዎን ማስገባት አለብዎ። ተቃውሞዎን ለማስገባት ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለገዎት ይህንን መጠየቅ ይችላሉ።

የተቃውሞ ደብደቤውን ወደ ተፈቀደለት ሰው በኢሜል ወይም በደብዳቤ ሊልኩት ይችላል። በትምህርት እና ስልጠና መምሪያው ድረ ገጽ ላይ የሚገኘውን አብነት ( template) መጠቀም ከፈለጉ እዚህ ማግኘት ይችላሉ።

ተቃውሞዎን በጽሁፍ ማቅረብ ካልፈለጉ፣ በምትኩ ተቃውሞዎን በቃል እንዲሰጡ መጠየቅ ይችላሉ። እርስዎን ወክሎ ሌላ ሰው ተቃውሞዎን እንዲያቀርብልዎ መጠየቅ ይችላሉ። ለምሳሌ የእርስዎ የአካል ጉዳት ድጋፍ ሰጭ ሰራተኛ ወይም አስተርጓሚ ሊሆን ይችላል።

## በትምህርት ቤቱ ውስጥ ልጅ ካለኝ፣ ቀጣይነት ያለው መመሪያን መከተል ስላለብኝ ልጀ ላይ ምን ይደርስበታል?

ትምህርት ቤትዎ መመሪያው በልጅዎ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ተጽእኖ እና እርስዎ ልጅዎን እንዴት ሊንከባከቡ እንደሚችሉ በጥንቃቄ አስቦበታል። መመሪያው እርስዎ ልጅዎን ከመንከባከብ ወይም ከትምህርታቸው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ከመሳተፍ ለማገድ የታቀደ አይደለም።

ትምህርት ቤትዎ መመሪያውን ከሰጠዎት በኋላ በተቻለ ፍጥነት 'የመገናኛ እና የመዳረሻ ፕሮቶኮል' ይሰጥዎታል። ይህም የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካትታል።

- ስለ ልጅዎ ትምህርት መረጃ እንዴት እንደሚደርስዎት
- ልጅዎ እንዴት ወደ ትምህርት ቤት መሄዱን እንደሚቀጥል እና ልጅዎ በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ በመልካም ሁኔታ እንዴት መሳተፍ እንደሚችል ይገልጻል
- ልጅዎ ተገቢውን ድጋፍ እና እንክብካቤ ማግኘቱን ለማረጋገጥ ምን እንደሚያደርጉ።

## መመሪያውን ካልተከተልኩ ምን ይደርስብኛል?

በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን ደንቦች ካልተከተሉ፣ መመሪያውን እንዲከተሉ ለማስገደድ ትምህርት ቤቱ ጉዳዮን ወደ ፍርድ ቤት ሊወስደው ይችላል።

ፍርድ ቤቱ መመሪያን ባለመከተል ስህተት እንደፈጸሙ ካረጋገጠ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- የገንዘብ ቅጣት ሊጥልብዎ ይችላል
- መመሪያውን እንዲያከብሩ ሊያዝዎት ይችላል
- መመሪያውን ለማክበር የተለየ እርምጃ እንዲወስዱ ሊያዝዎት ይችላል
- ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛውንም ነገር እንዲያደርጉ ሊያዝዎት ይችላል።

መመሪያውን ባለመከተልዎ አይታሰሩም፣ የወንጀል ሪከርድ አይመዘገብብዎትም ወይም የወንጀል ቅጣት አይጣልብዎትም።

## የተጣለብኝ መመሪያ እንዲቀር ከፈለኩኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?

መመሪያው ውስጥ የተካተቱት ደንቦች እንዲነሱ ወይም እንዲቀየሩ ከፈለጉ መመሪያውን የጣለብዎትን የተፈቀደለት ሰው እነዚህን ለውጦች እንዲያደርግ መጠየቅ ይችላሉ። የተፈቀደለት ሰው ይህንን ለማድረግ ከተስማማ፣ የተሻሻለውን መመሪያ ቅጂ በጽሁፍ ሊሰጡዎት ይገባል። የተፈቀደለት ሰው በጥያቄዎ ካልተስማማ ቀጣይነት ያለው መመሪያ እርስዎ ላይ ለመጣል ሲወስኑ የተጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ መስፈርቶችን መከተል አለባቸው።

የተፈቀደለት ሰው በመመሪያው ላይ አዲስ ህጎችን መጨመር ከፈለገ ቀጣይነት ያለው መመሪያ እርስዎ ላይ ለመጣል ሲወስኑ የተጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ መስፈርቶችን መከተል አለባቸው።

## በተጣለብኝ መመሪያ ላይ ይግባኝ ማለት ከፈለኩ ምን ማድረግ አለብኝ?

እርስዎ ላይ የተጣለብዎን መመሪያ ወደ ትምህርት ቤትዎ ይግባኝ ብሎ ለማመልከት የሚከተሉት ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡

- እርስዎ ላይ መመሪያ መጣሉን የማይስማሙ ከሆነ
- የተፈቀደለት ሰው በመመሪያው ውስጥ የሆነ ነገር እንዲቀይርልዎ ጠይቀው ነገርግን ጥያቄዎ ተቀባይነት ካላገኘ እና እርስዎ በዚህ ውሳኔ ደስተኛ ካልሆኑ
- የተፈቀደለት ሰው መመሪያውን ከቀየረው እና እርስዎ በዚህ ውሳኔ ደስተኛ ካልሆኑ

- የተፈቀደለት ሰው መመሪያውን ላለመሰረዝ ከወሰነ እና እርስዎ በዚህ ውሳኔ ደስተኛ ካልሆኑ

የውስጥ ግምገማ ውሳኔ ማመልከቻው ወደ ርዕሰ መምህሩ ከተላከበት ጊዜ ጀምሮ 28 ቀናት ሊወስድ ይችላል። ይህ ጊዜ መመሪያው በእርስዎ ላይ እንዲጣል ያስቻሉ ምክንያቶችን እንደገና ለማጤን እና በተቃውሞ ደብዳቤዎ ላይ ያቀረቧቸውን ምክንያቶች በጥንቃቄ ለመገምገም ይጠቅማል።

የውስጥ ገምጋሚው ግለሰብ መመሪያውን ሊለውጠው፣ ሊሰርዘው ወይም ከሁለቱ አንዱን ላያደርግ ይችላል። ውሳኔ ላይ ከተደረሰ በኋላ ውሳኔውን ለመረዳት ይረዳዎ ዘንድ የውስጥ ግምገማ ውጤት ላይ ለመድረስ ያበቁትን ምክንያቶች በኢሜል እና/ወይም በፖስታ የምክንያቶች ቅጂ ይደርስዎታል።

በውስጥ ግምገማው ውጤት ደስተኛ ካልሆኑ፣ ውሳኔውን ለቪክቶሪያ ሲቪል እና የአስተዳደር ልዩ ፍርድ ቤት ይግባኝ (Victorian Civil and Administrative Tribunal) ማለት ይችላሉ። ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ መረጃ እዚህ በትምህርትና ስልጠና መምሪያ ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

## አስተርጓሚ (በቃል እና በጽሁፍ) ወይም ሌላ ድጋፍ ሰጭ አካል/ሰው ከፈለኩስ?

አስተርጓሚ (በቃል እና በጽሁፍ) ወይም ድጋፍ ሰጪ ሰው ከፈለጉ፣ ይህንን ለትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር ቢነግሩት(ሯት) ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ ሊረዱዎት ይችላሉ።

ልጅዎ የመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር (የምትማር) ከሆነ፣ የትምህርት እና ስልጠና መምሪያውን ክልላዊ ቢሮን በማነጋገር ተጨማሪ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

| | |
|---|---|
| ሰሜን ምስራቅ ቪክቶሪያ (North Eastern Victoria)<br>ስልክ: 1300 333 231<br>ኢሜይል: nevr@education.vic.gov.au | ሰሜን ምዕራብ ቪክቶሪያ (North Western Victoria)<br>ስልክ: 1300 338 691<br>ኢሜይል: nwvr@education.vic.gov.au |
| ደቡብ ምስራቅ ቪክቶሪያ (South Eastern Victoria)<br>ስልክ: 1300 338 738<br>ኢሜይል: sevr@education.vic.gov.au | ደቡብ ምዕራባዊ ቪክቶሪያ (South Western Victoria)<br>ስልክ: 1300 333 232<br>ኢሜይል: swvr@education.vic.gov.au |

## ተጨማሪ መረጃ ብፈልግስ?

የበለጠ መረጃ ለማግኘት የትምህርት እና ስልጠና መምሪያውን ድረ ገጽ እዚህ መጎብኘት ይችላሉ።